በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከኖቬምበር 1-10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም ከኖቬምበር 11-20 እና ከኖቬምበር 21-30 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2024

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ....- 1 -
ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች ....- 2 -
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....- 4 -
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት....- 4 -
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ....- 4 -
የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር....- 4 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....- 5 -
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....- 5 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ..- 6 -
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....- 6 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ....- 7 -
ካርታ6 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 8 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ....- 9 -
ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21-30, 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 9 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 10 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 10 -



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

በኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ተስተውሏል፡፡ በሌላ በኩል ወቅታዊውን ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ የሚያገኙት የደቡብ፣ የደቡብ ምሥራቅና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት ዝናቡ በቦታና በመጠን ረገድ የተሻለ ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት ለዝናብ መፈጠር መንስኤ የሆኑት የአየር ሁኔታ ገጽታዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ በመጠናከራቸው ምክንያት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ የተመዘገበ ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎች ላይም ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ እንዲሁም የደመናው ሽፋን ወደ መካከለኛውና ሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች በመስፋፋት በጥቂት ቦታዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንዲጥል አስተዋፅዖ አድርጓል። ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በቢሾፍቱ 33.8፣ በመተሐራ 58.1፣ በነገሌ 36.1፣ በነቀምቴ 33.0፣ በአዲግራት 55.0፣ በአሶሳ 43.8፣ በአዋሽ አርባ 55.0 እና 60.0፣ በቡለን 30.5፣ በጊዳ አያና 39.7፣ በጊኒር 64.0፣ በሀረሪ 37.0፣ በሆሳዕና 45.0፣ በሊሙ ገነት 44.6፣ በመኤሶ 34.0 እንዲሁም በወራቤ 96.0 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ እምብዛም ያልተጠናከረ ቢሆንም፤ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም በአዲግራት 5.0፣ በአምባ ማርያም 4.0፣ በቡኢ 5.0፣ በደባርቅ 5.0፣ በደብረ ብርሃን 2.4፣ በጅግጅጋ 4.0፣ በመሀል ሜዳ 3.2፣ በሾላ ገበያ 1.2፣ 4.0 እንዲሁም በወገል ጤና 2.9 በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ15 የተለያዩ የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40.6-96.0 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል በመተሐራ፣ በአዲግራት፣ በአሶሳ፣ በአዋሽ አርባ፣ በጊኒር፣ በሆሳዕና፣ በሊሙ ገነት እንዲሁም በወራቤ ይጠቀሳሉ (ምስል 1) ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል:nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ የመካከለኛው ትግራይ ምስራቃዊው ክፍል እና የምስራቅ ትግራይ፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብና የማዕከላዊ ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም፣ የደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ ዞን፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሊባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሃረርጌ ዞኖች፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ እንዲሁም ቦረናና ምስራቅ ቦረና፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ የየም ልዩ ዞን እና ሀላባ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከሶማሌ የሲቲ፣ የፋፈን፣ የኤረር፣ የሸበል፣ የሊበን፣ የዳዋና የአፍዲር ዞኖች፤ አዲስ አበባ እንዲሁም




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ከ6-120 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ2-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ከትግራይ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ፣ የመካከለኛው፣ የሰሜን፣ የምስራቅና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን ጎንደርና ዋግህምራ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል የማሂ፣ ፈንቲ፣ ቅልበቲ እና አውሲ ዞኖች እንዲሁም ከሶማሌ የነጎብ፣ የጃረር የቆራሄ እና የዶሎ ዞኖች ላይ ከ5 ሚ.ሜ በታች ከ2 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር የምስራቅ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ ጎንደር ምስራቃዊው ክፍል እና የማዕከላዊ ጎንደር ምዕራባዊው ክፍል፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም፣ የደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲና ፋንቲ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ምዕራብ ሃረርጌ ዞኖች፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ እንዲሁም ቦረናና ምስራቅ ቦረና፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ የየም ልዩ ዞን እና ሀላባ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከሶማሌ የአፍዲር፣ የፋፈንና ሊበን ዞኖች፣ የኤረር፣ የነጎብና የሸበል ምዕራባዊው ክፍል እና የሲቲ ምስራቃዊው ክፍል ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት



የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከረጅም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር

ከመደበኛ በታች   መደበኛ   ከመደበኛ በላይ


ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በሌላም በኩል በመካከለኛዉና በሰሜን ምስራቅ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የነበረው እርጥበት ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍርፍሬ ተከሎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች ጠቀሜታ ነበረው። በአንጻሩም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ እንዲሁም ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት በተለይም በደጋማው አካባቢ በቦረናና ጉጂ ዞኖች ለተዘሩ ሰብሎች ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ሲሆን በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልና የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማችት ገንቢ ሚና ነበረው (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞግቤ፤ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ እና የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል፡፡ በተለይም የመካከለኛው እና በታችኛው አባይ፣ የላይኛው ኦሞግቤ እና የ መካከለኛው ገናሌ ዳዋ ና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ነበራቸው፡፡ ይህም የእርጥበት ሁኔታ በየተፋሰሶቹ በሚገኙ ግድቦች፣ ሰው ሰራሽ የውሃ መያዥያዎች እንዲሁም የከርሰ ምድር እና የገጸ ምድር የውሃ አቅምን ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በአንጻሩ ግን አብዛኛው የተከዜ እና የአፋር ደናክል ተፋሰሶች በደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ ምሥራቅ፣ መካከለኛው እና ደቡብ አከባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ይዘወተራል፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ፤ ደቡብ ምስራቅ እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በሚቀጥሉት ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀጣይነት የሚኖራቸው ሲሆን፤ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋና ሰፊ ቦታዎችን የሚያካትት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 6)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ወላይታ፣ ኮንሶ፣ ጌዲኦ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፤ አሌ፣ አማሮ እና ቡርጂ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ከፋ፣ ቤንች ሸኮ፣ ዳዉሮ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበል፣ ኖጎብ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ ፋፋን፣ ኤረር እና ጃረር፤ እንዲሁም ሀረሪ እና ድሬዳዋ ዞኖች ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ እንዲሁም ከክረምት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ ባሉት አከባቢዎች ማለትም ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ ወለጋ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር  አኝዋክ እና ማዥንግ ዞኖች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡

በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በተለይም ከሳምንቱ አጋማሽ በኋላ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከአማራ ክልል በምዕራብ፤ ሰሜን፣ ማዕከላዊና ደቡብ ጎንደር፤ ምስራቅ፤ ምዕራብ እና ሰሜን ጎጃም፤ አዊ ዞኖች እና ባህርዳር ዙሪያ፤ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፤ ሰሜን ሸዋ፣ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ፤የምዕራብ፣ የደቡብና የደቡብ ምስራቅና ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ፋንቲ፤ ማሂ፣ ሃሪ፣ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፤ አዲስ አበባ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች በተለይም በጥቂት ቀናቶች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6)፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡




ካርታ6 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713   ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር የሶስተኛዉ አሥር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ(ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋና ሰፊ ቦታዎችን የሚያካትት ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 7)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፤ በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)፡፡

Total Rainfall (mm) 21-30,Nove 2024




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21-30, 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር ሁለተኛው አስር ቀናት የሚኖረው እርጥበት ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለተዘሩ እንደ ሽንብራ እና ጓያ ለመሳሰሉት የጥራጥሬ ሰብሎች የተሟላ እድገት እንዲኖራቸዉ ከማድረግ አንፃር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በቦረናና ጉጂ ዞኖች ለተዘሩ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። እንዲሁም ውሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ከመኖሩ ጋር ተያይዞ በመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል አርሶ አደሮችም ሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ልዩ ትኩረት በመስጠት የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብና በአግባቡ የመከመር ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር ሁለተኛዉ አሥር ቀናት በገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ኦጋዴን፣ በላይኛው እና መካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ በታችኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት የሚያገኙ ሲሆን፤ በተጨማሪም በመካከለኛው አባይ፣ በጥቂት መካከለኛው አዋሽ እና በታችኛው ተከዜ ላይ መጠነኛ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ይህን ሁኔታ ተከትሎ በተለይም የውሃ እጥረት ባለባቸው እና በቆላማ ንዑስ ተፋሰሶች ላይ የሚገኘውን እርጥበት የውሃ አቅርቦት እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ አዋሽ እና የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች በደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ስር ይቆያሉ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et